# በጎነት ለአብሮነት

የገሃዱ ዓለም ፍጥረታት በተፈጥሯቸውና በባህርያቸው በርካታ ልዩነቶችን ያስተናግዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ አጥፊ እና ጠፊ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ተመጋጋቢ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ሌላው ቀርቶ እንዲረዳዱ ወይም እንዲተጋገዙ ሆነው የተፈጠሩት በተቃራኒነት ተሰልፈው አንዱ አንዱን ሲጎዳው ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ ቀዳሜ - ፍጥረት አዳም (አደም ) ከተፈጠረ በኋላ ሔዋን (ሐዋ) የተፈጠረችው እንዲረዳዱ እና አብረው በፍቅር እንዲኖሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ከእነርሱ አብራክ የተገኙት ልጆች ካለመግባባት የተነሳ ሞትን ያክል ፀረ-ሕይወት ሊያመጡ ችለዋል ፡፡

እንደሚታወቀው ሰው በሳይንስም ሆነ በመንፈሳዊ እውቀት ሲመዘን አስተዋይ እና አርቆ አሳቢ የፍጥረታት የበላይ እንደሆነ በድርሳናት እና በታሪክ እንረዳለን፡፡ ታዲያ ሰው ይህን የበላይነቱን ባግባቡ ባለመጠቀሙ እኩይ ተግባራትን ሲፈጽም ይታያል፡፡ አንዳንዶቹ የተባረኩትና የተመረጡት በተቃራኒው ለሰው ልጅ የሚበጅ፣ ሰላምን የሚሰጥና ችግርን የሚያቃልል መልካም ስራ እያከናወኑ በትሩፋታቸው በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡ የትኛው ይሻላል? ለማለት እምነትንም ሆነ ሳይንስን ሙጥኝ ብለው የማይኖሩ ሰዎች ያሉትን እንመልከት፡፡

"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፣

ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም፡፡" ብለው ይተርታሉ፡፡

ከዚህ አባባል በመነሳት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማህበረሰቡ ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ለማየት እንሞክራለን ፡፡ መጀመሪያ የበጎ ስራ (በጎ ፈቃድ አገልግሎት ) ምንነትን በመጠኑ ዳሰስ ስናደርግ፦ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማኅበራዊ ኃላፊነትን በአግባቡ በመወጣት የሚከሰቱትን ማኅበራዊ ችግሮች ተረባርቦ በራስ አቅም የመፍታት ተግባር ነው:: በጎ ፈቃድ ማዕድ በማጋራት፣ የአቅመ-ደካሞችን ቤት በመሥራትና የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት፣ ትምህርት ቤቶችንና የጤና ተቋማትን በመገንባት፣ የችግረኛ ገበሬዎችን እርሻ በማረስ፣ አረም በማረም፣ አካባቢን አረንጓዴ በማድረግ እና በሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚገለጽ ነው::

በጎነት ስስትን ሳይሆን መስጠትን፣ ጥላቻን ሳይሆን ፍቅርን፣ እኔነትን ሳይሆን እኛነትን፣ በጋራ መቆምንና መተሳሰብን የሚፈጥር ነው፡፡ ይህን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ

ብሄራዊ የማህበረሰብ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማብሠሪያ ፕሮግራም ላይ እንደገለጹት "በጎነት የሚባለው ለራሱ መልካም ስራ  መስራት ሳይሆን የራሱን ጊዜ፣ እውቀትና ሀብት ለሌላ ወገን በመስጠት የሚገለጽ ነዉ ። ይህም የፍልስፍና መሠረት አለው፡፡ አልትሩዚም ይባላል፡፡ ትርጉሙ ሰው ከእንስሳት የሚለየው ማሰብ መቻሉ ብቻ ሳይሆን ራሱን ሰውቶ ለሌሎች መልካም ለማድረግ የሚተጋ ፍጡር በመሆኑ ነው፡፡ የበጎ ፈቃድ አገለግሎትን ለመስራት በቀዳሚነት የሚሳተፉት ወጣቶች ከመሆናቸዉ ጋር ተያይዞ ወጣቱ ውስጥ እሳት አለ፤ እሳቱን ለልማት ለማዋል ጥንቃቄን ይጠይቃል፡፡ ይህ ማለት በወጣቱ ዘንድ ያለውን የተደበቀ ጉልበት በብልሀትና በጥበብ መገልገል ካልቻን ለጥፋት ይውላል" ነው ያሉት፡፡

ከጠቅላዩ መልእክት ስንወጣ ይህን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በርካታ የርዳታ ደርጅቶች፣ ባለሀብቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በትብብር እውን እንደሚያደርጉት ይታወቀል፡፡ ለአብነት አንድ ልጥቀስ ቀደም ሲል ምዕራብ ጀርመን የተባለ የአውሮፓ ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ አማራ ክልል ላይ የህጻናት ማሳደጊያ (orphanage) በሚል ስም ድርጅት አቋቁሞ መማር የማይችሉ ወገኖችን እንዲማሩ አድርጓል፡፡ አሠራሩም ለእያንዳንዱ ልጅ በስሙ የራሱ መለያ ቁጥር ተሰጥቶት በዚያ መሠረት አስፈላጊውን በጀት የሚልክ አሳዳጊ አለው፡፡ ከዚያም ድርጅቱ የአስተዳደር ሠራተኛ ቀጥሮ ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ለተማሪዎች አሟልቶ ከአንደኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ አስተምሮ ለቁም ነገር አብቅቷል፡፡ በዚህ ድርጅት ያደጉ በርካታ ምሁራንም በየስራ ዘርፉ ተሰማርተው ወገናቸውንና ሀገራቸዉን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ይህን መልካም ተግባር ያከናወኑ አካላት በዘር፣ በዜግነት፣ በቀለምና ወዘተ ግንኙነት የሌላቸው መሆናቸው ደግሞ ጉዳዩን የበለጠ ልዩ ያደርገዋል፡፡

በክርስትናም ሆነ በእስልምና እምነት አስተምህሮ ለሰዎች በተለያየ ምክንያት መርዳት እንደሚያስፈልግና በፈጣሪ ዋጋ እንደሚያስገኝ በሰፊው ይገለጻል፡፡ ይህ ስርዓት ዘፈቀደ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቅዱስ ቁርአን ተጽፎ የሚገኝ ነው፡፡ በዚህ ዓለምም ቢሆን መልካም ሰርቶ ያለፈ በስራው ታሪክ ሲዘክረዉ ይኖራል፡፡ መጥፎ የሠራውም ለዘላለም የታሪክ ተወቃሽ ይሆናል፡፡ ሁሉም እንደ ሥራው ስለሚከፈለው ምንም ይሁን ምን በጎነት ይጠቅማል እንጅ አይጎዳም፡፡

ይህን ቅዱስ ተግባር እንደመነሻ በመውሰድ የክልሉ መንግሥት በየዓመቱ በርካታ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራ በዕቅድ እንዲመራ በማድረግ እያከናወነ ይገኛል፡፡ ለአብነት በ2016 በጀት እስከ ነሀሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 8 ነጥብ ሦስት ሚሊየን የኀብረተሰብ ክፍሎችን በበጎ

ፈቃድ አገልግሎት ለማሠማራት እቅድ 5 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በጎ ፈቃደኞችን ለሥራ ማሰማራቱን ከክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ከዚህ ውስጥ የወጣቱ ድርሻ ሦስት ሚሊየን 44 ሽህ 568 ነው:: በእቅድ ዘመኑ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል፡- ችግኝ ተከላ 441 ሚሊየን፣ - አዲስ የቤት ግንባታ 590፣ - ነባር ቤት እድሳት 887፣- ሰብል በመሥመር መዝራት 31 ሽህ 628 ሄክታር፣ - ደም ልገሣ አራት ሽህ አሥር ዩኒት (ሰዎች)፣ - የገጠር መንገድ ጥርጊያ (ጥገና) 262 ኪሎ ሜትር፣ - የከተማ ፅዳት (ቦይ ማፋሰስ) አንድ ሽህ 148 ኪሎ ሜትር ፣ ማዕድ ማጋራት ለ9 ሽህ 878 ኀብረተሰብ፣ - እየተማሩ ላሉ 19 ሽህ 952 ተማሪዎች 18 ሽህ 988 ደርዘን ደብተርና 11 ሽህ 055 ፓኮ እስክርቢቶ ድጋፍ መደረጉን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ከዚህ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወጣ ያለ አስተሳሰብ እና ተግባር ሲኖር ማህበረሰቡን ሊጎዳው ይችላል፡፡ አንድ ግለሰብ ሌላውን በቀላል ነገር ይጣላውና ይጎዳዋል፡፡ ለምሳሌ በክልላችን አንድ ሰው በሆነ አጋጣሚ አንድን ሰው ቢገድል ደም ምለሳ እየተባለና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ግድያው ማቆሚያ የለውም፡፡ በተቃራኒው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ግን አንዱ ሌላውን እንደ ራሱ ወይም ከዚያ በላይ በመውደድ ችግሩን ያቃልለታል፡፡ ያም የተረዳ አካል በሚችለው ይረዳዋል፤ ካልቻለም እድሜ ጤና ይለምንለታል፡፡ ይህን በጎ ስራ የሚያከናውን ሰው ህይወተ - ሥጋውና ህይወተ - ነፍሱ ይለመልማል፤ መንፈሳዊ እርካታም ያገኛል፡፡ የስነ - ልቦናና የሞራል ሀሴት በውስጡ ይሞላል፡፡ ዋጋው ደግሞ በምድር ብቻ ሳይሆን ከሰማይ በላይ ነው፡፡ እንደዚህ አንዱ ለአንዱ በጎ ቢያስብ ይህ የእርስ በርስ ግጭት አይፈጠርም ነበር፡፡ ስለዚህ ይህ ተግባር ለሰላም ያለው ሚና ከፍ ያለ ስለሆነ ሁላችንም በዚህ ሀሳብና ተግባር ተቃኝተን ልንሠማራ ይገባል እላለሁ፡፡ ምክንያቱም ለሰላም፣ ለፍቅርና ለአንድነት ፍቱን መድኃኒት ነውና፡፡ ይህ መልካም ሥራ ለዘላለም ይቀጥል እያልሁ ለዛሬው ከዚህ ላይ ይብቃኝ፡፡ ሰላም!!

**ዝግጅት በፍሬው ምናለ**

ስም ቀሲስ ፍሬው ምናለ

ፊርማ ----------------

ቀን -----------------